DENVER PUBLIC SCHOOLS
Discover a World of Opportunity™

# የፈተናዎች መመሪያ ለወላጆች

ACCESS 2.0 (Assessing Comprehension and Communication in English State to State) ( የእንግሊዝ ክልል እስከ ክልልመረዳትን መመርመር እና መግባባት)

ፈተናዎች ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለትምህርት ባለሙያዎች ተማሪዎች በክፍል ደረጃቸውን ሚጠበቅበትን እውቀት ስለማወቅ አለማወቃቸው እና ለ 21ኛው መ/ክ/ዘ ዝግጁ ሆነው ለመመረቅ ስለመቻላቸው ጠቃሚ መረጃ ይሰጣሉ። እነዚህ የፈተና ውጤቶች በልጅዎ ትምህርታዊ መሻሻል ማስረጃ አካል ውስጥ አንድ ልኬትን ለማቅረብ የታቀዱ ናቸው።

## ይሄ ፈተና ምንድን ነው?

ACCESS 2.0 አመታዊ ግምገማ ሲሆን ይሄም ግምገማ የእንግሊዘኛ ቋንቋ እድገት በማህበራዊ እና ትምህርታዊ በሆኑ አከባቢዎች በመስማት ፣ በማንበብ ፣ በመፃፍ እና በመናገር ላይ የሚደረግ መመዘኛ ነው የክልላዊ ግምገማ ሲሆን የእንግሊዘኛ ተማሪዎችነን ለመቆጣጠር የፌደራል መመዘኛዎችን የሚያሟላ ግምገማ ነው የእንግሊዝኛ ተማሪዎች ተብለው የተለዩ ከ K-12 ባሉ ክፍሎች የሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ ይህንን ምዘና በየዓመቱ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል።

ልጆት መዋለ ህፃናት ውስጥ ከሆነ/ች አራት ክፍሎችን የያዘ ፈተናን በወረቀት እና በእርሳስ ይፈተናሉ ልጆት ከ 1-12 ከሆነ/ች ግምገማው ሙሉ በሙሉ ኦንላይን ላይ ሲሆን፣ በወረቀት መፈተን ወይም ኦንላይን የፅሁፉን ዋናውን ክፍል በወረቀት ፈተናው ላይ በመጨረስ ሊሆን ይችላል

ከ 1ኛ -12ኛ ባሉ ክፍሎች ውስጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተብለው የተለዩ እና ጉልህ የአእምሮ ስንክልና ያለባቸው ተማሪዎች በተለዋጭ ACCESS ለ ELLs (Alternate ACCESS for ELLs) ውስጥ ይሳተፋሉ። ይህ ፈተና ሙሉ በሙሉ በወረቀት ላይ የሚሰጥ ነው።

ለሁሉም የክፍል ደረጃዎች በወረቀት ፈተናውን መፈተን ለሚፈልግ ተማሪ የፅሁፍን ፈተና ጨምሮ ይሰጣል

## ልጄ የሚፈተነው መቼ ነው?

ACCESS 2.0 የሚሰጠው ከጃኑዋሪ - ፌብሩዋሪ ሲሆን ለብዙ ተማሪዎች ኦንላይን ምዝገባ ይሰጣል ስለልጅዎ የፈተና ጊዜ ሰሌዳ ለማወቅ የልጅዎን ት/ቤት ያነጋግሩ። ልጅዎ እንደየ ክፍል ደረጃው/ዋ እና የትምህርት ዓይነቱ በተወሰኑ ቀናት ብቻ ይፈተናል/ትፈተናለች፤ በመላው የፈተና ወቅት አይሆንም። ትክክለኛውን የጊዜ ሰሌዳ ለማወቅ የልጆትን አስተማሪ ያናግሩ።

## ልጄ ምን ውጤት (ቶች) ይቀበላል?

ሜይ ላይ ለወላጆች የልጆቻቸውን ብቃት የሚገልፅ የውጤት ሪፖርት ወደ ቤታቸው ይላከላቸዋል የልጆትን በድምር የ8 ውጤቶች ይቀበላሉ ውጤቶቹም በ 6 የብቃት ደረጃን ይገልፃሉ

| 1 - መግባት | 2- ተለይቶ መታየት | 3 - ማደግ | 4 - ማስፋፋት | 5 - ማገናኘት | 6 - መድረስ |
|---|---|---|---|---|---|

ለመስማት ፣ ለማንበብ፣ ለመፃፍ እና ለመናገር ያለውን ተለይቶ ውጤቱ ይደርሳችኋል ከዚህ፣ የሚከተሉት ጥምር ነጥቦች ተገኝተዋል

- የቃል ቋንቋ – መናገር (50%) እና ማዳመጥ (50%) ያጣምራል
- ማንበብና መጻፍ – ንባብ (50%) እና መጻፍ (50%)
- መረዳት – ማዳመጥ (30%) እና ንባብ (70%)
- ጠቅላላ ውጤት - ማዳመጥ (15%)፣ መናገር (15%)፣ ንባብ (35%) እና መጻፍ (35%)

## እነዚህ ነጥቦች ጥቅም ላይ የሚውሉት እንዴት ነው?

የACCESS 2.0 ውጤቶች አስተማሪዎችን የእያንዳንዱ ተማሪ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት እዲያውቁ ይረዳል ይሄ ለተማሪዎች ተገቢ የሚሆን የመመሪያ አይነትን ለማወቅ እገዛ ያደርጋል አንድ የእንግሊዘኛ ተማሪ በመደበኛ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክፍሎች ለመመደብ ብቁ የሚሆነው መቼ እንደሆነ ለመወሰን ያግዛል ተማሪዎች ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት አገልግሎቶች ለመውጣት 4.0 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ አጠቃላይ የብቃት ደረጃ እና 4.0 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የማንበብ እና መጻፍ መለኪያ ነጥብ ሊኖራቸው ይገባል።

## ተጨማሪ መረጃ

በልጅዎ ትምህርት ውስጥ እንዲሳተፉ እናበረታታዎታለን። እባካችሁ የልጅዎን አስተማሪ በማናገር ልጆችን ቤት ውስጥ እንዴት መርዳት እንዳለባችሁ እና ፈተናውን ለመውሰድ የሚጠቅማቸው ነገሮች እንዲሟላላቸው ለማድረግ ከመጠየቅ ወደኋላ አይበሉ።

**ተጨማሪ መረጃ፡- WIDA**

- ይህንን https://www.wida.us/downloadLibrary.aspx, ይጫኑና በደረጃዎች ርዕስ ስር ያለውን ከቤተሰብ ዌቢናር ይመልከቱ

**ተጨማሪ መረጃ፡- ፈተናዎች**

ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፡

- http://assessments.dpsk12.org
- 

ፈተናውዎች ላይ ጥያቄዎች ወይም ስጋት ካለዎ፣ እባክዎ የልጅዎን ት/ቤት በቀጥታ ያናግሩ ወይም የቤተሰብ ተወካይ አገልግሎትን በ (720) 423-3054 ደውለው ያነጋግሩ።